**ወልቂጤ ዩንቨርሲቲ**

**የማህበራዊ ሳይንስ እና ስነሰብ ኮሌጅ**

**የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል**

# የነገስታት ገፀባህሪይ አሳሳል ንፅፅር ከ "ንጉስ አርማ ህ" እና "የመጨ ረሻዉ ንጉስ ቀ.ሀ.ስ " ታሪካዊ ተዉኔቶች አንፃር

በ

ስንታየሁ ፀጋዬ

**ወልቂጤ ዩንቨርስቲ**

**ሰኔ 13/2014 ዓ.ም**

# የነገስታት ገፀባህሪይ አሳሳል ንፅፅር ከ"ንጉስ አርማ ህ" እና " የመጨ ረሻዉ ንጉስ ቀ.ሀ.ስ" ታሪካዊ ተዉኔቶች አንፃር

**በ**

ስንታየሁ ፀጋዬ

**የጥናቱ አማካሪ**

መምህርት ዳናይት ብርሀኑ

**ለትአትር ጥበባት ትምሀርት ክፍል** ለዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፁሁፍ

**ወልቂጤ ዪኒቨርስቲ**

**ሰኔ 13/ 2014 ዓ.ም**

## የአማካሪዉ ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ፁሁፍ በወልቂጤ ዩነቨርስቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ መስፈርት መሰረት ድጋፍ የተደረገለት መሆነን አረጋግጣለሁ።

የአማካሪዉ ስም ..........................................................................

ፊርማ________________________________________

ይህ በተማሪ ስንታየሁ ፀጋዬ  የነገስታት ገፀባህሪይ አሳሳል ንፅፅር  "በንጉስ አርማህ " እና " የመጨረሻዉ ንጉስ ቀ.ሀ.ስ " ታሪካዊ ተዉኔቶች አንፃር የመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፁሁፍ ሲሆን የዩንቨርስቲዉ ጥራት ደረጃ ያ ሟላና በቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ማረጋገጫ ነዉ።

ፈታኝ  አንድ ----------------------------------------------------- ፊርማ

ፈታኝ  ሁለት------------------------------------------------------ፊርማ

ቀን --------------------------

# ምስጋና

በመጀመሪያ አስጀምሮ ላስጨረሰኝ ሁሉንም ፈፃሚ ለሆነዉ ለድንግል ማርያም ልጅ ለሆነዉ ለእግዛብሔር ክብር ምስጋናየ ይድረሰዉ። እንዲሁም ለእናቴ ገዳምየ ፣ ለህይወት አበራ ፣ለትግስት (ማሚ)፣ለራሔል ፈቀደ እንዲሁም ደከመኝ ሰለቸኝ ስል ከጎኔ ሁናችሁ ላበረታችሁኝ ጓደኞቼ እጅግ የከበረ ምስጋናየ ይድረሳችሁ ።

# አበርክቶ

ደስታዋን ፣ ፍቅሯን እና ሙሉ ህይወቷን ለእኔ ትታ ለዚህ ላደረሰችኝ ለእናቴ ገዳምነሽ አበበ ይሁንልኝ።

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ፁሁፍ የመጨረሻው ንጉስ የቀ.ሀ.ስ ታሪካዊ ተዉኔት እና በንጉስ አርማህ ታሪካዊ ተዉኔትላይሲሆን የነገስታት ገፀባህሪይ አሳሳል ንፅፅር በንጉስ አርማህ እና በመጨረሻዉ ንጉስ ቀ.ሀ.ስ ታሪካዊ ተዉኔቶችአንፃር በትንታኔ መልክ የሚያቀርብ ሲሆን በገላጭ የጥናት ዘዴ የተሰራ ነዉ። ይህ ጥናታዊ ፁሁፍ አጥኝዋበምትሰራበት ጊዜ የተለያዩ መረጃዎችን የተጠቀመች ሲሆን ተዉኔቶችን ደጋግማ በማንበብ ፣ ለጥናቱየሚያግዙ መፅሀፎችን እና ጥናታዊ ፁሁፎችን በመጠቀም ከነገስታት ገፀባህሪይ አሳሳል ንፅፅር አንፃርተንትናለች። የታሪካዊ ተዉኔቶች ነገስታት በገፀባህሪይ አሳሳል መንገዶች ሁሎችም የተገለፁ ሲሆኑ ሁለቱንንጉሶች በገፀባህርያት አሳሳል መንገዶች ከተነተነች በኋላ ከገፀባህሪያት አሳሳል ንፅፅር ተተንትኗል።

# ማውጫ


ምዕራፍ  አንድ........................................................................................................1

1  መግቢያ ..............................................................................................................1

1.1 የጥናቱ ዳራ.......................................................................................................2

1. 2  የጥናቱ  አላማ .................................................................................................2

1. 2. 1  አብይ አላማ..................................................................................................2

1. 2. 2   ንዑስ አላማ ..................................................................................................2

1. 3   የጥናቱ  ጠቀሜታ ............................................................................................2

1. 4  የጥናቱ  መጠነ ርዕይ(ወሰን)................................................................................3

1.5 የጥናቱ ዘዴ........................................................................................................3

1.7 የ ጥናቱ አወቃቀር...............................................................................................3

1.8 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች...........................................................................4

ምዕራፍ ሁለት.......................................................................................................5

2. ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት ............................................................................................5

2.1. የ ታሪክ ምንነት ................................................................................................5

2.2. የ ታሪካዊ ተውኔት ምንነት...................................................................................5

2.2. የንፅፅራዊ ጥናት ምንነት......................................................................................7

2.4. የገፀባህርያት ምንነት ..........................................................................................7

2.5. የገፀባህርያት አሳሳል ..........................................................................................8

2.5.1 አካላዊ አሳሳል ደረጃ..........................................................................................8

1.5 .2  ማህበራዊ አሳሳል ደረጃ.....................................................................................9

1.5 .3 ስነ-ልቦናዊ አሳሳል ...........................................................................................10

2.5.4  ሞራላዊ አሳሳል ደረጃ .......................................................................................10

2 .3 የተዛማጅ ስራውች ቅኝት...................................................................................11

3. የነገስታት ገፀባህሪይ አሳሳል  ንፅፅር  ከ"ንጉስ አርማህ"  እና ....................................12

3.1  የንጉስ  አርማህ ታሪካዊ  ተዉኔት ትንተና..............................................................12

3.1.1 የንጉስ አርማህ ታሪካዊ  ተዉኔት ጭምቅ ታሪክ ......................................................12

3. 1. 2  የንጉስ አርማህ ገፀባህሪይ ትንተና ከገጸባሃሪያት አሳሳል አንጻር ...................................12

3.1.3 የንጉስ አርማህ አካላዊ አሳሳል................................................................................12

3 . 1 . 4  የንጉስ አርማህ ማህበራዊ አሳሳል.......................................................................13

3.1. 5 የንጉስ አርማህ ስነ-ልቦናዊ አሳሳል .......... 14
3. 1.6 የ አርማህ የሞራልላዊ አሳሳል .......... 15
3.2 የመጨረሻ ንጉስ የቀ.ሀ.ስ ተዉኔት ትንተና .......... 17
3.2.1 የመጨረሻ ንጉስ የቀ.ሀ.ስ ተዉኔት ጭምቅ ታሪክ .......... 17
3. 2.2 የመጨረሻዉ ንጉስ የ ቀ.ሀ.ስ ገፀባህሪይ ትንተና ከገጸባሃሪያት .......... 17
3.2.3.የቀ.ሀ.ስ አካላዊ አሳሳል .......... 17
3.2.4 የቀ.ሀ.ስ ማህበራዊ አሳሳል .......... 18
3.2.5 የ ቀ.ሀ.ስ ስነ -ልቦናዊ አሳሳል .......... 21
3.2.6 የቀ.ሀ.ስ ሞራላዊ አሳሳል .......... 22
3.3 የንጉስ አርማህ እና የንጉስ ቀ.ሀ.ስ የገፀባህሪ ይአሳሳል ንፅፅር እና ግምገማ .......... 23
ምዕራፍ አራት .......... 24
4 ማጠቃሊያ እና የመፍትሔ ሀሳቦች .......... 24
4. 1 ማጠቃለያ .......... 24
4.2 የመፍትሔ ሀሳብ .......... 25

# ምዕራፍ አንድ

## 1 መግቢያ

ስነፁሁፍ የሰው ልጅ ለት ከለት የኑሮ ሁኔታቸውን እና ገጠመኞችን የሚያንፀባርቅበት መሳያ ነው፡፡*"ስነ ፁሁፍ የሰውን ልጅ ሀዘን፤ደስታን ፤ጥላቻ፤ፍቅር ድልና ሽንፈት ፤ረሀብ እና ጥግብ ምኞት እና ጉስቁልና፤ ውድቀት እና ብልፅና ፤ህይወት እና ሞት እንዲሁም ሰናይ እና እኩይ ባህሪያቱን የህይወትገፅታዎችን የማሳየት ሀቅም አለው። የስነ ፅሁፍ ምንጩም አፍላቂውም ተቀባዩም ሰው በመሆኑ ማህበራዊነቱ የጎላ ነው።"*

*(ዘሪሁን አስፋው ፤ የስነ ፅሁፍ መረታውያን ፤1998፡7)*

ስነ ፁሁፍ በውስጡ ብዙ ዘርፎችን የያዘ ሲሆን ከዘርፎቹ መካከልም አንዱ ተውኔት ነው።ተውኔት በገሀዱ አለም እለት ከእለት እየተከናወኑ ያሉ እንቅስቃሴዎችን እንዲሁም ረጅም ታሪክ ያላቸውን በጊዜና በቦታ ተወስኖ እንዲሁም ገፀባህሪያትን በመፍጠር በገፀባህሪያት አጅቦ ለተመልካች በመድረክ ላይ እንዲመለከቱት እና እንዲሰሙት አድርጎ የሚያቀርብ ነው፡፡*"ተውኔት የሰውን ልጆች የእለት ከለት ገጠመኝ አስመስሎ እየቀዳ በጊዜ እና በቦታ ተወስኖ የሚመደረክ ነው። ተውኔት ወይንም ድራማ የሚለው ቃል "ደራን"ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙም "ማድረግ ወይንም መከወን" ማለት ነው። አርስቶትል የተውኔት ምንነት ባጭሩና እምቅነት ባለው መልኩ ሲገልፅ "ተውኔት ከሰው ልጆች እውነተኛ ድርጊት የሚከተብ የኪነ ጥበብ ዘርፍ ነው።" ይለዋል።*

*(ፋንታሁን እንግዳ ፤ የተውኔት አፃፃፍ ዘዴ ፤ 1990፡8)*

ተውኔት በውስጡ ብዙ ዘውጎችን በመያዝ ተመልካቾችን ያዝናናል ፤ያስተምራል፤ ቁምነገር ያስጨብጣል። ከተውኔት ዘውጎች ውስጥ እያዝናና ያለፉ ታሪካችን እያሳወቀ የሚያልፈው አንዱ የተውኔት ዘውግ ታሪካዊ ተውኔት ነው።ታሪካዊ ተውኔት ያለፉ ታሪኮችን የድርጊታቸውን፤የክዋኔወቻቸውን ቅደም ተከተል በመጠበቅ የስነፁሁፍ ዘርፍ ወደሆነው ተውኔት በመቀየር ላለውና ለመጪው ትውልድ ታሪኩን በትክክል እንዲረዱት እና እንዲያውቁት ለማድረግ በመድረክ እያዝናና እና እያስተማረ ያሳያል።

ኢትዮጵያ ከቀደምት እስካሁን ባለው ዘመናት ብዙ ታሪክ ያላት ሀገር ናት ።በሀገሪቱ በውስጥም ብዙ የተፈፀሙ ታሪኮች ወደ ተውኔት ተቀይረው ብዙዎቹ በመድረክ ላይ ለተመልካች እና ለንባቢያን በመፅሀፍ ለመቅረብ በቅተዋል። ይህ ጥናታዊ ፁሁፍ በመልካሙ ዘሪሁን ተፅፎ ፤ በማንያዘዋል እንደሻው በመዘጋጀት በብሄራዊ ትያትር ቤት በ1993 ዓ.ም በቀረበው በንጉስ አርማ ታሪካዊ ተውኔት ላይ እና በ2010 ዓ.ም በትግስት አለማየሁ የተፃፈውን የመጨረሻው ንጉስ በቀዳማዊ ሀ/ስላሴ ታሪካዊ ተውኔት ላይ ነው። ጥናታዊ ፁሁፉም በንጉስ አርማ እና በቀዳማዊ ሀይለ ስላሴ የነገስታት የገፀ ባህሪ አሳሳል ንፅፅር ላይ የሚተነተን ይሆናል።

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ሀገራችን ለታሪካዊ ተውኔቶች የሚሆን አጀብ የሚያሰኝ ታሪኮች ያላት ሀገር ስትሆን አንዳንድ ፀሀፊያንም ያለፈ ታሪኮችን በማንበብ ለትውልድ መደረስ አለበት ያሉትን ታሪክ ወደ ተውኔት በመቀየር ለተመልካቾች አድርሰዋል ።ለተመልካች ከቀረቡት መካከል የተወሰኑትን ስንመለከት፡- የቴወድሮስ ራዕይ፣ ቴወድሮስ፣የቃቄ ወርዶት፣ ህንደኬ፣ አሉላ አባ ነጋ፣ ወ.ዘ.ተ… መጥቀስ እንችላለን።

ከዚህም በተጨማሪ ደራሲያን ወደ ተውኔት ያልተቀየሩ ታሪካችን ወደ ተውኔት ሲቀይሩ ስለ ባለታሪኮች ማንነት፣ በዛን ዘመን ምን እንደሚመስሉ፣ ምን ሲስሩ እንደነበር ወ.ዘ.ተ… ትክክለኛ ታሪካቸውን በመፃፍ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ያደርጋሉ፣ ይህን ጥናታዊ ፁሁፍ አጥኝዋ ለማጥናት ያነሳሳት በመጨረሻው ንጉስ ቀዳማዊ ሀ/ስላሴ ታሪካዊ ተውኔት እና በንጉስ አርማህ ታሪካዊ ተውኔት መካከል ስላለው የነገስታት ገፀባህሪይ አሳሳል ንፅፅር የተሰራ ጥናትዊ ፁሁፍ ባለመኖሩ ፣ በሁለቱ ንጉሶች ያለውን የነገስታት ገፀባህሪይ አሳሳል ንፅፅር ማድረግ እና በነገስታት ገፀ ባህሪይ አሳሳል ንፅፅር ላይ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ማድረግ ስለምትፈልግ ነው።

## 1. 2 የጥናቱ አላማ

### 1. 2. 1 አብይ አላማ

የዚህ ጥናታዊ ፁሁፍ አብይ አላማው በመጨረሻው ንጉስ በቀዳማዊ ሀ/ስላሴ ታሪካዊ ተውኔት እና በንጉስ አርማህ ታሪካዊ ተውኔት ላይ የነገስታት ገፀ ባህሪይ አሳሳል ንፅፅር ትንታኔ መስጠት ነው።

### 1. 2. 2 ንዑስ አላማ

የዚህ ጥናታዊ ፁሁፍ ንዑስ አላማዎች፡-

- በመጨረሻው ንጉስ በቀዳማዊ ሀ/ስላሴ ታሪካዊ ተውኔት ውስጥ የሚገኘውን የቀዳማዊ ሀይለ ስላሴ ገፀባህሪይ አሳሳል ማሳወቅ።
- በንጉስ አርማህ ታሪካዊ ተዉኔት ውስጥ የሚገኘውን የንጉስ አርማህ ገፀባህሪይ አሳሳል ማሳወቅ
- ነገስታትን ከገፀባህርያት አሳሳል አንፃር ማነፃፀር እና መገምገም

## 1. 3 የጥናቱ ጠቀሜታ

የዚህ ጥናታዊ ፁሁፍ ጠቀሜታው፡-

- በታሪካዊ ተውኔቶች ውስጥ ያሉት ነገስታት በገፀባህሪያት አሳሳል ደረጃወች እንዴት እንደተሳሉ ለማወቅ ይጠቅማል።
- በተውኔቶች ውስጥ የገፀባህሪያት አሳሳል ንፅፅር እና ግምገማ ሲደረግ ለወደፊት ለሚፅፉ ደራሲያን በድርሰታቸው ውስጥ ገፀባህርያትን በደንብ እንዲቀረፁ ያደርጋል።
- ለቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለዲግሪ ማሟያነት ይጠቅማል።

- በተጨማሪም ሌሎች አጥኝወች በዚህ ጥናት ዙሪያ መረጃ ቢፈልጉ እንደማጣቀሻነት ይጠቅማል።

## 1. 4 የጥናቱ መጠነ ርዕይ(ወሰን)

ይህ ጥናታዊ ፁሁፍ ትኩረት አድርጎ የሚሰራው በመልካሙ ዘሪሁን የተፃፈውን የንጉስ አርማህ ታሪካዊ ተውኔት እና በትግስት አለማየሁ የተፃፈውን በመጨረሻው ንጉስ ቀዳማዊ ሀይለ ስላሴ ታሪካዊ ተውኔት ላይ ሲሆን ሁለቱን ተውኔቶች ከነገስታት ገፀባህሪይ አሳሳል ንፅፅር አንፃር መተንተን ብቻ ላይ የተወሰነ ነው።

## 1.5 የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናታዊ ፁሁፍ የሚጠቀመው ገላጭ የአጠናን ዘዴ ሲሆን አለም እሸቱ "መሰረታዊ ምርምር እና የዘገባ አፃፃፍ" ላይ እንደገለፀው ገላጭ ምርምር ገለፃን ፣ትንታኔ እና አተረጓጎም መሰረት የሚያደርግ ሲሆን በሁለቱም ተለዋዋጭ መካከል የሚኖረውን ተዛምዶ እያወዳደረ እና እያነፃፀረ መመልከት ይችላል ። በዚህ ሂደት ውስጥ መረጃዎችን ከተለያዩ ምንጮች የሚያሰባስብ ሲሆን ትኩረቱ ግን የአንድ ተጨባጭ ሁኔታ ትክክለኛ ባህሪ መግለፅ ወይም ማሳወቅ ይሆናል። (1994፡48) አጥኝዋ ይህን ጥናታዊ ፁሁፍ ለመስራት የተለያዩ የመረጃ ዝዴዎችን ተጠቅማለች። ከተጠቀመቻቸው መካከል ፡-

- ሁለቱን ታሪካዊ ተውኔቶችን በማንበብ ፣
- ለጥናቱ የሚያግዙ መፅሀፍ በ ማንበብ እና
- በዚህ ጥናታዊ ፁሁፍ ዙሪያ የተሰሩ ጥናታዊ ፁሁፎችን በማንበብ የነገስታት ገፀባህሪ አሳሳል ንፅፅር ከ " ንጉስ አርማህ" እና" የመጨረሻው ንጉስ ቀዳማዊ ሀ/ ስላሴ" ታሪካዊ ተውኔቶችን ተንትናለች ።

## 1. 6 ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄወች

- በመጨረሻው ንጉስ ቀዳማዊ ሃይለ ስላሰ ታሪካዊ ተውኔት ውስጥ ያለው ንጉሳዊ ገጸ ባህሪይ እንዴት ተገለፀ?
- በንጉስ አርማህ ታሪካዊ ተውኔት ውስጥ ያለው የንጉስ ገጸ ባህሪይ በገጽ ባህሪይ የአሳሳል ደረጃውች እንዴት ተገለፀ?
- የንጉስ አርማህ እና የቀሀስ ገፀባህሪይ አሳሳል ንፅፅር እና ግምገማ ሲደረግ ምን ይመስላል?

## 1.7 የ ጥናቱ አወቃቀር

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ በውስጡ አራት ምዕራፎችን የያዘ ነው። ምዕራፍ አንድ ፡-መግቢያ፣የጥናቱ ዳራ፣የጥናቱ አላማ፣ የጥናቱ መጠን ርዕይ፣ጥናቱ የሚያሳያቸው ጥያቂዎች፣ የጥናቱ አወቃቀር እና በጥናቱ ወቅት

ያጋጠሙ ችግሮችን የያዘ ሲሆን በምዕራፍ ሁለት ፡-የንድፍ ሃሳብ ቅኝት እና በተዘማጅ ቅኝት ጹሁፎች ላይ ያተኩራል።በምዕራፍ ሶስት ፡-በዋናነት የጥናቱ ክፍል የሚተነተንበት ሲሆን በምዕራፍ አራት ፡-የጥናቱን መደምደሚያ፣የመፍሔ ሀሳብ እና ዋቢ መጽሀፍት ያጠቃልላል።.

## 1.8 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

አጥኝዋ በጥናቱ ወቅት ያጋጠሟት ችግር ፡-

- በዩኒቨርስቲዉ ዉስጥ በርዕሱ ዙሪያ  ያሉት መፅሀፎች ዉስን መሆናቸዉ፣
- ጥናቱ የሚሰራበት የንጉስ አርማህ ታሪካዊ ተዉኔት አለመገኘት እንዲሁም የተለያየ ፁሁፍ መሆን፣
- መረጃወችን በተፈለገበት ጊዜ አለማግኘት፣
- አጥኝዋ ከሰዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የተውኔቱን ባለቤት የሆነዉን መልካሙ ዘሪሁንን በማነጋገር እና ከሌሎች ሰዎች ጋር እርዳታ በመጠየቅ ችግሮችን በመቅረፍ መስራት ችላለች።

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት

### 2.1. የ ታሪክ ምንነት

ሰዎች ተወልደው እስኪሞቱ ድረስ ብዙ ተግባራትን አከናውነው ያልፋሉ። ታድያ ይህ ተግባራቸዉ ታሪክ ወይም የህይዎት ታሪክ ተብሎ ይገለጻል።ታሪክ ስንል መረጃወችን በመጠቀም ሰዎች በህይዎት ዘመናቸው ካሳለፏቸው ክንውኖች እየተነሳን አጠር ባለ መልኩ ሰድረን የምናስቀምጠው ክፍል ነው። በአጠቃላይ ታሪክ የክንዋኔዎች ስብስብ እና ላለፉት ዘመናት የተከወኑ ታሪኮችን ግልጽ በሆነ መልኩ የሚያብራራ ነው። ፋንታሁን እንግዳ ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያነዎቻቸው ‘’ከሃ እስከ ፐ’’ በተሰኘው መጸሃፉ እንደሚከተለው አስፍሯል።

> “ ታሪክ በጊዜ ቅደም ተከተል መሰረት ከ አንዱ ድርጊት ቀጥሎ የትኛው ድርጊት የትኛ
>
> ው ድርጊት እንደሚከተለው ለማሳዎቅ ይጠቅማል።
>
> ታሪክ በማንኛውም ተውኔት ድርጊት ክንዋኔ በጊዜ ቅደም ተከተል ተዘርዝሮ የ
>
> ሚቀመጥ ነው።
>
> ታሪክ የክንዋኔዎች ስብስብ በመሆኑ በማንኛውም የፈጠራ ስራ ማለትም ለተውኔቱ
>
> ለረጂም ልብወለድ፣ ለ አጭር ልብወለድ፣ ለ ፊልም ለተራኪ ግጥም እና ለ ልዩ ልዩ
>
> ተረቶች መሰረት ነው ተብሎ ይታመናል።’’(1993፣55)

### 2.2. የ ታሪካዊ ተውኔት ምንነት

ታሪካዊ ተውኔት ለ አንድ ሃገር ወይም ለህዝብ ያለፉ ታሪኮችን ወደ ተውኔት በመቀየር ለተመልካች በመድረክ እና ለአንባብያን በመጻፍ የሚያስተላልፍ ነው።ታሪካዊ ተውኔት ከ አንድ እዉነታ ተነስቶ የፈላስፋወች፣ የ ምሁራኖችን፣ የነገስታትን፣ የልዑላን ወ.ዘ.ተ በአጠቅላይ ዘመናቸው ጥሩም ሆነ መጥፎ ተግባራቸው በጸሃፈ ተውኔቶችም ሆነ በታሪካዊ ተውኔቱ ፀሃፊዎች ለመድረክ በሚያሞች መልክ ተፅፎ ሲቀርብ ታሪካዊ ተውኔት እንለዋለን። ታሪካዊ ተውኔት በዛን ዘመን የነበረውን ትክክለኛ ሁኔታ ሳይቀር የድርጊቱን ቅደም ተከተል በመጠበቅ በትዉልድ ወደ ትዉልድ በተውኔት መልኩ የሚስተላለፍ አንዱ የተውኔት ዘውግ ነው። ፋንታሁን እንግዳ ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው "ከ ሃ እስከ ፐ" በተሰኘው መፅሀፉ እንደ ሚከተለው አብራርቷል።

‘’ይህ የተውኔት ዘውግ በእዉነተኛ ታሪካዊ ሰዎች በተለይም በታላላቅ ነገስታት፣ የ

ጦር ጀነራሎች፣ በሃይማኖት ሰዎች፣ በከያንያን፣ በስፖርተኞች፣ እና በሌሎች ታሪካዊ ግለሰቦች

የ ህይወት ታሪክ ላይ የሚመሰረት ነው።’’(1993፣54)

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ለሃገራችን ኢትዮጵያ ህዝቦች ታሪክን ወደ ተውኔት በመቀየር ለህዝቦች ታሪካዊ ተውኔቶችን የደረሱ ደራስያን አሉ። እነዚህ ደራስያንም የሚደርሱት ታሪካዊ ተውኔትም በሃገራችን በጦር፣ ለነገስታት፣ በታላላቅ የእምነት አባቶች ወ.ዘ.ተ…የተደረጉ እና በዚህም ትልቅ ተፅዕኖ ፈጥረዋል የሚሏቸውን ሰዎች ታሪክ በማስታወስ ወይንም በማንበብ ታሪካቸውን የሚከትቡ ተውኔቶችን ፅፈውላቸዋል። ለአብነት በሃገራችህን ደራሲዎች የተፃፉ ታሪካዊ ተውኔቶችን ብንመለከት፦ “ቴዎድሮስ” የተሰኘው ታሪካዊ ተውኔት በሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን፣ “የቴዎድሮስ ራዕይ” የተሰኘው ታሪካዊ ተውኔት በጌትነት እንየው፣ “የንጉስ አርማህ” የተሰኘው ታሪካዊ ተውኔት በመልካሙ ዘሪሁን ወ.ዘ.ተ… ተውኔቶችን መጥቀስ እንችላለን። እንዷለም አስቻለዉ "ንግስት ዘዉዲቱ" ታሪካዊ ተዉኔት በተሰኘዉ መፅሐፍ ስለ ታሪካዊ ተዉኔት እንደሚከተለዉ አብራርቷል ፡-

" ታሪካዊ ተዉኔት ገፀባህሪያትን በአካል፣ በማህበራዊ ፣ በኢኮኖሚያዉ ፣

በፖለቲካዊ ተሳትፎቸዉ የምናዉቃቸዉ እና የማናዉቃቸዉ ሊሆኑ ይችላሉ ።

የታሪካዊ ተዉኔት ገፀባህሪያቱም በገሀድ አለም መፈጠር እንደሚቻል ልብ

ማለት ያስፈልጋል ። በታሪካዊ ተዉኔት የስም አሰጣጥ እና ዉክልና

ሌላዉ ትኩረት ሊሰጥ የሚገባዉ ነጥብ ነዉ ። የዋና ዋና ገፀ ባህሪያት

ስም እንዳለ ሁኖ በተዘዋዋሪ በማህበረሰብ ዘንድ ሁለት መልክ

( በአሉታዊ ወይም በአወንታዊ )ያላቸዉን የታሪክ ሰዎች ይኖራሉ ።" (2010፣5)

ከላይ እንደተገለፀዉ በተዉኔቱ ዉስጥ የምናገኘዉ ገፀባህሪያት በትክክለኛ ተሳትፎ የምናዉቃቸዉም የማናዉቃቸዉም ይሆናሉ ይህ ማለት በ ታሪካዊ ተውኔት ዉስጥ በታሪኩ የማናውቃቸው ገፀባህርያት ለታሪኩ ማስከጃ ተብለው ሊገቡ ይችላሉ። ገፀባህርያት በተውኔት ዉስጥ የሚቀረፁት በተለየ ጀብዳቸው ወይንም በተለየ ባህሪያቸው የሚያስደንቁ ሁነው ነገር ግን በደካማ ጎናቸውም ተስለው ይቀርባሉ። እንዲሁም በተውኔቱ ዉስጥ የሚሳሉት ገፀባህርያት የትክክለኛ ባለታሪኩ ስም ፣ የነበሩትን የአነጋገር ለዛ፣ ስሜትን ወ.ዘ.ተ… በያዘ መልኩ ተቀናብረው ይቀርባሉ። ይህም በእንዲህ እንዳለ በታሪካዊ ተውኔት ዉስጥ የሚኖሩ ገፀባህርያት ከትክክለኛው ታሪክ ተሳታፊወች ቁጥራቸው እንደሁኔታው ሊቀነስም ሊጨመርም ይችላል። ነገር ግን ደራሲው ታሪካዊ ተዉኔቱን በሚፅፍበት ጊዜ ዋናውን የእዉነተኛ ታሪክ ፍሰት ወይንም እዉነታ ማዛባት ብሎም የመደምሰስ መብት የለዉም።ይህም የሚሆነው እዉነተኛ ታሪኩ ለትዉልድ

መተላለፍ ስላለበት እና የአሁኑ ትዉልድ ካለፈው ትዉልድ የሚማረው ጠንካራ እና ደካማ ጎን በመኖሩ ነው።

## 2.2. የንፅፅራዊ ጥናት ምንነት

ንፅፅራዊ ጥናት በሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ነገሮችን ከያዟቸው እና ከሸፈኗቸው ነገሮች ጋር እያስተያየን እና እያነፃፀረ የሚያጠና የጥናት አይነት ነው። ንፅፅራዊ ጥናቶች በምርምር ቴክኒኮች እና ስልቶች ላይ የተመሰረተ ትንተና ተያያዥነት ያላቸው ተመሳሳይነትን ወይንም ልዩነትን ይተነትናል። ይህ ጥናት በሁለት እና ከዚያ በላይ በሆኑ ነገሮች ላይ ተመስርቶ ነገሮች ያላቸውን አንድነት እና ልዩነት ለማወቅ የሚደረግ ጥናት ነው። ያለው እንዳወቅ ``የምርምር መሰረታዊ መርሆች እና አተገባበር`` በተሰኘው መፀሀፉ እንደሚከተለው አብራርቷል።

> “ይህ ጥናት ንድፉ የአንድ ሰው ወይንም ቡድን ባህርይ የተለያየ ተለዋዋጮችን
>
> በመመርኮዝ ያለውን ወጥነት ለመወሰን ወይንም በሁለት እና ከዛ በላይ ሰወች
>
> ወይንም ቡድኖች የባህርይ መመሳሰል እና መለያየት ለማጥናት ያስችላል።( 1998 ፤39)

ከዚህ እንደምንረዳው ይህ ንፅፅራዊ ወይንም አወዳዳሪ የአጠናና ምንነት በብዛታቸው ከሁለት በላይ የሆኑትን ነገሮች በተለያየ መዓዘን እየተመለከተ እና እያወዳደር የሚያጠና ሲሆን እነዚህን ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑትን ነገሮች አጥኚው በሚወስንላቸው ህግ ወይንም ተመሳስሎነት አልያም ልዩነቶች እያነፃፀረ ለማጥናት የሚያስችል የጥናት አይነት ነው። የንፅፅራዊ ጥናት ዋና አላማ የሚነፃፀሩት ወይንም የሚወዳደሩት በ መካከላቸው ያለውን ክፍተት አልያም ተምሳሌት ወይንም ልዩነት የመሰሰሉት ጉዳዮች ምክንያታቸው ምን እንደሆነ እያወዳደሩ ለመገምገም ነው። ንፅፅራዊ ጥናት በቴአትር ላይ አጥኚው ከሚነሳበት ርዕስ አንፃር አንዱን ከሌላኛው ጋር ያወዳድራል ማለት ነው። ታዲያ አጥኚው ለነዚህ ዝግጅቶች የተለያዪ መስፈርቶችን እያነሳ ይፈትሻል ምልክት ነው ።

## 2.4. የገፀባህርያት ምንነት

ገፀ ባህርያት አንድ ደራሲ፣ ገጣሚ፣ሰአሊ፣ፀሃፊ ሃሳቡን ለመግለፅ ታሪኩን ለማስጀመርም ለማስጨረስም የ ሚፈጥራቸው አካላት ናቸው።ገፀ ባህርያት ሲሳል በ ታሪኩ ዉስጥ ተስለው የሚገኙ ሰወች፣ እንሰሳት፣ ግኡዝ ነገሮች፣ መንፈሶች፣ ረቂቅ ነገሮች ገፀባህሪወች ተብለው ይቆጠራሉ። ስለዚህም በስዕል፣ በ ግጥም፣ በ ፅሁፈተ ተውኔትም፣ በልብወለድ ይሁን በማንኛውም ኪነጥበባዊ ዘርፍ ዉስጥ ተቀርፀው ወይም ተስለው ያሉ ገፀባህርያት ታሪኩን የሚያስከትሉት የታሪኩ ፈፃሚወች እና አድራጊወች ናቸው።

የሻው ተሰማ በ``ተውኔት አፅናፍ መነፅር`` በተሰኘው መፅሃፉ ዉስጥ እንደሚከተለው አብራርቶታል።

> “በ አካል፣ በ ቀለም፣ በምግባር፣ በስም በ አድራሻ በመሳሰሉት የ አንድ ፍጥረት

መከሰቻ እና መታወቂያ መስፈርቶች ለይተን የምናውቃቸው እና ነጥለን የምንጠራቸው፤ በ

ፈጠራ ስራ ዉስጥ ተጨባጭ ሚና የሚጫወቱ ምናባዊ ፍጥረታት ናቸው።”(1998፣48)

## 2.5. የገፀባህርያት አሳሳል

የገፀባህርያት አሳሳል ገፀባህርያቱን በእዉኑ አለም ላይ አሉ ተብሎ እስኪታመን ድረስ በጥንቃቄ ተስለው ( ተቀርጸው) ለተመልካች የሚቀርቡበት ዘዴ ነው። ደራሲ ሰዎችን ወይንም ግኡዝ ነገሮችን ገፀባህርይ ብሎ ሲሰይማቸው አንባብያን እንዲረዷቸው በገሃዱ አለም ያሉትን ነገሮች ያማከለ መሆን አለበት። በዚህም መሰረት አራት የገፀባህርይ አሳሳል ደረጃዎችን ይጠቀማል። አካላዊ የገፀባህርይ አሳሳል፣ ማህበራዊ የገፀባህርይ አሳሳል፣ ስነ ልቦናዊ የገፀባህያት አሳሳል፣ ሞራላዊ የገፀባህርይ አሳሳል ሲሆኑ በነዚህም መሰረት ገፀ ባህርያቱን መቅረፅ ይኖርበታል። ጫንያለዉ ወ/ጌወርጊስ እና ሌሎቹ " መሰረታዊ የተዉኔት አፃፃፍ መርሆች " በሚለዉ መፅሀፍ ስለ ገፀባህሪ አሳሳል እንደሚከተለዉ አስፍሯል ፦

" የገፀባህሪያት አሳሳል የምንለዉ አንድ የተዉኔት አፃፃፍ መርህ ሲሆን

የሰዉ ልጅ ባህሪያቶች ገፅታ በተዉኔት መስታዉትነት የሚያቀርብ

ቴክኒኪን የሚያሳይ ነዉ። በርግጥም የመጀመርዉ ገፀባህሪይ

(ድርሰቱ ዉስጥ ያሉ ሰወች ) አሳሳል ወይንም አቀራረብ መሰረቱ

የሰዉ ልጅ ማንነት የማሳወቅ እጥረት መሆኑ ግልፅ ነዉ ።

ምክንያቱም የሰዉ ልጅ ማንነት ለማሳየት በቅድሚያ ያንን የሚያሳዩት

ገፅታ ማወቅ ቀዳሚ ተግባር ነዉ እና በመቀጠልም ነዉ "ይህንን ማንነት

እንዴት አድርጌ በተዉኔት አማካኝነት በመድረክ ላቅርበዉ ?

የሚል ጥያቄ የሚያነሳዉ ።"(2006 ፣19)

### 2.5.1 አካላዊ አሳሳል ደረጃ

አካላዊ የገፀባህሪ አሳሳል ደረጃ በአንድ ድርሰት ዉስጥ ገፀባህሪያት የሚኖሩበትን አካባቢ የጊዜና የማህበራዊ እውነታን ወይንም የመቼት ገለፃን ተከትሎ በቀጣይነት ለታዳሚ ግንዛቢ የሚበቃ የገፀባህሪያት አሳሳል መንገድ ነው። ፈንታሁን እንግዳ “የተውኔት አጻጻፍ ዘዴ”በተሰኘው መፅሐፍ እንደሚከተለው አብራርቷል።

“በዚህ የአሳሳል ደረጃ የእያንዳንዱ የገጸባህሪይ

አለባበስ ፣ፆታ፣ እድሜ ፣እንቅስቃሴ፣ ጤና፣ መልክ

ማለትም ጥቁረት፣ ንጣት፣ ጠይምነት፣አቋምን ማለትም

ውፍረትን፣ ቅጥነትን፣ እርዝመትን ፣እጥረትን ምን እንደሆነ ያብሰሰራራል።（1990፣ 27）

ከዚህ በተጨማሪ የጸጉራቸው ፣አኳኋን የፊታቸው ፣የፊታቸው፣የአይናቸው፣የእጃቸው አፈታጣጠር፣ አቋቋማቸውን ይመስላ? የሚለብሷቸው ልብሶች፣በእጃቸው የሚይዟቸው እቃዎች . . .ወዘተ ሊጠቀስ ይችላሉ። በተጨማሪም ፋንታሁን እንግዳ ከ ሀ እስከ ፐ በሚለዉ መፅሐፍ ዉስጥ ስለ አካላዊ አሳሳል እንደሚከተለዉ ቀርቧል ።

"የአንድን ገፀ ባህሪ አካላዊ አሳሳል ጀረጃ ሲባል የገፀ ባህሪዉ ፆታ ሴት፣ወንድ የገፀባህሪዉ እድሜ ህፃን ፣ወጣት፣ ጎልማሳ፣አዛዉንት የገፀባህሪዉን መልክ ወይም ቀለም ቀይ ፣ጥቁር፣ ነጭ እና የመሳሰሉት የተዉኔቱን ሀሳብ እና መቼቱን አስረግጦ መተንተን። (1993. 82)

### 1.5 .2 ማህበራዊ አሳሳል ደረጃ

ማህበራዊ አሳሳል ደረጃ ተጨባጭነት ያለው የአገላለጽ ዘዴ ነው። ማህበራዊ አሳሳል የምንለው ገፀባህሪይው በሚኖርበት አለም ውስጥ ያለው ማህበራዊ፣ባህላዊ፣ሀይማኖታዊ ና በተሰበዋ ነገሮችና ሚናወችን ሁሉ አካቶ የያዘ ነው። ፋንታሁን እንግዳ " ዝክረ ተውኔት " በተሰኘው መጽሃፍ እንደ ሚከተለው አብራርቱል።

*“እንድ ጋብቻ ፣የጤና ሁኔታ፣የልዩ ልዪ ማህበራዊ ተቋማት ያለው ተሳትፎ፣ ሃብታምና ድህነት፣ የ ሀይማኖትና ፖለቲካ አቋምን፣ የተሰማሩበትን የ ሙያ መስክ ወይንም ዘርፍ የመሳሰሉት ይገኛሉ። (1990፤104)*

እንዲሁም አባትና እናት፣የቤተሰቡ ሁኔታ፣ስንት ልጅ እንደወለደ ፣የእሱ እና የቤተሰቡ የሀይማኖት ሁኔታ፣ ስለ ትዳሩ፣ስንት ልጅ ወልዷልና፣ ስንት ሚስት አግብቱዋል፣የሚኖርበት ቤት ምን ይመስላል፣በቤቱ ውስጥ የሚጠቀምባቸው እቃዎች ምን ይመስላሉ ወ. ዘ .ተ ..የመሳሰሉትን ይይዛል።”ከዚም በተጨማሪ ፋንታሁን እንግዳ ከ`` ሀ እስከ ፐ`` በተሰኘዉ መፅሐፍ ስለማህበራዊ አሳሳል እንደሚከተለዉ አስፍሯል ፡-

" ማህበራዊ አሳሳል ደረጃ የገፀ ባህሪዉ ምጣኔ ሀብት ፣የሙያ መስክ ሀይማኖት፣ቤተሰባዊ ዝምድና እና ሌሎች ገፀባህሪዉ በአካባቢያዊ ተፅዕኖ ስር የሚወድቁባቸዉን ነገሮች ሁሉ አካቶ ይይዛል ። ማህበራዊ የአሳሳል ደረጃ እንደ አካላዊ የአሳሳል ደረጃ ሁሉ ነባራዊ የአሳሳል ደረጃ በመባል ይታወቃል ።"(1993 ፣32)

### 1.5 .3 ስነ-ልቦናዊ አሳሳል

ስነልቦናዊ አሳሳል በተጨባጭነት ውስጣዊ ስሚቶች ማለትም በህሊናዊ ጉዳቶች ላይ ተመርኩዞ የገጸ ባህሪያት አቀራረጽ አይነቶች ሲሆኑ በደራሲያን ዘንድ እስከሲሁዎቹ የገጸባህሪያት አሳሳል ድረጃ ሁሉ በበለጠ ሁነታ ተቀባይነት ያላቸው ናቸው። ፋንታሁን እንግዳ ``ዝክረ ተውኔት`` በተሰኘው መጽሃፍ እንደሚከተለው አብራርቱዋል።

*"ይህ ያሳሳል ደረጃ የሚያተኩረው የ ገጸባህሪውን ልዩ ልዩ ምኞት፣ ተስፋዎች፣*

*የመጥላት ና የመፋቀር ስሚቶች፣ስለ ድርጊቶች፣በ ድምሩ ስሚታዊነት እና*

*አስተዋይነትን ሁሉ በመቅረጽ የጉጸባህሪያቱን ህሊናዊ መስክ የሚናሳይበት መንገድ ነው።"*

*(1990፣105*)

ስነልቦናዊ አሳሳል አይተን የምንገምተው ሳይሆን ውስጣዊ ፍላጎት እና ግብ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። እንዲሁም በአይናችን አይተን ብቻ መግለጽ የምንችለው ሳይሆን ከውስጥ ያለዉን የተደበቀውን ወይንም መመርመር የሚጠይቅ የአሳሳል ክፍል ነው። ሳሙኤል ተስፋየ "የትወና ጥበብ " በሚለዉ መፅሐፍ ስለ ስነ ልቦናዊ እንዲህ ገልፆታል ፦

" የገፀባህሪዉ ፍላጎቶች ፤መጥላት እና መዉደዱ ፣

ፍቅሩና ጥላቻዉ ፣ ሀዘን እና ደስታዉ ፣ፍንደቃዉ እና

የቅስሙ መሰበር ሁሉ በዚህ ስብዕናዉ ምክንያት

ይወሰናል ።"( 2010 ፣ 55 )

### 2.5.4 ሞራላዊ አሳሳል ደረጃ

ሞራላዊ አሳሳል የአንድን ገጸባህሪይ የውስታዊ አመለካከት ማለትም መልካምነቱን ወይንም መጥፎነቱን ፣ ጥሩነቱን ወይንም ኩነኔውን፣ቸርነቱን ንፉግነቱን ፣ጉረኛነቱን ትሁትነቱን፣ድል የማያደርግ እና የማሸነፍ ወ.ዘ .ተ… የመሳሰሉትን የምንገልጽበት ነው። ፋንታሁን እንግዳ"ዝክረ ተውኔት " በተሰኘው መጽሃፍ እንደሚከተለው ይብራራል።

*"ሞራላዊ አሳሳል በሰው ልጆች ፍጥረት የመከራ እና የመዋረድ*

*የሞራል ጥያቄ ላይ መሰረት በማድረግ የሚነሳ ተፈትሮ ከፈቀደው*

*በታች ወርዶ ቅጥያጣ ስግብግብ ሆኖ ሲቀርብ ከሚገባው በላይ ክብር ፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወይንም ከሁሉም በተቃራኒ አለማዊና መንፈሳዊ መርሆችንና ህጎችን ተቀብሎ የሞራል አስተማሪ ሲሆን በሚያሳዩት ና በመሳሰሉት ፍረ ሀሳቦች ላይ ያነጣጥራል።"(1990፣105)*

## 2 .3 የተዛማጅ ስራውች ቅኝት

አጥኝዋ ከዚህ ጥናት ጋር የተሻለ ቅርበት ያላቸው በርካታ ጥናታዊ ጹሁፎችን ማግኘት ባትችልም ያገኘቻቸውን ጥናታዊ ጹሁፎችን ከጥናቱ ጋር ያላቸውን አንድነት እና ልዩነት እንደ ናሙናነት ታቀርባለች ።

በአብነት ጌታቸው ግንቦት 1991 ዓ.ም የገጸባህሪያት አሳሳል ደረጃወች ንጽጽራዊ ምልከታ በ"ያላቻ ጋብቻ" እና በ "ከርሞ ሰው"ተውኔቶች የሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለቋንቋወች ጥናት ተቋም ለትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጹሁፍ ነው። ይህ ጥናታዊ ጹሁፍ ከዚኛዉ ጥናታዊ ፁሁፍ የሚለይበት በሁለቱ ተውኔቶች ውስጥ ያሉትን ሁለት ሁለት ገፀባህሪይ በማዉጣት ከገፀባህሪያት አሳሳል ንፅፅር አንፃር ሲያጠና ከነገስታት ገፀባህሪይ አሳሳል ንፅፅር በንጉስ አርማህ እና በመጨረሻው ንጉስ ቀ.ሀ.ስ ታሪካዊ ተውኔቶች አንፃር ደግሞ ሁለቱን ንጉሶች በገፀባህሪያት አሳሳል ንፅፅር ሲያደርግ ሁለቱም ጥናታዊ ፁሁፎች አንድ የሚያደርጋቸው የገፀባህርያት አሳሳል ንፅፅር ላይ መጠናታቸዉ ነዉ።

በአስመላሽ አኒቶ ሰኔ 2010 ዓ.ም የ"ንጉስ አርማህ" ታሪካዊ ተውኔት ከንጉስ አርማህ እውነተኛ ታሪክ ጋር ሲነጻጸር " በሚል ርዕስ ለወልቂጤ ዩኒቨርስቲ ለትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለድግሪ መሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጹሁፍ ነው ።

ይህ ጥናታዊ ፁሁፍ የንጉስ አርማህን ታሪካዊ ተውኔት ከትክክለኛ ታሪካቸው ጋር ማነፃፀር ላይ ያተኮረ ሲሆን ከነገስታት ገፀባህሪያት አሳሳል ንፅፅር አንፃር በንጉስ አርማህ እና በመጨረሻዉ ንጉስ ቀ.ሀ.ስ ታሪካዊ ተዉኔቶች አንፃር ደግሞ ሁለቱን ንጉሶች በገፀባህሪያት አሳሳል ንፅፅር ሲያደርግ ሁለቱም ጥናታዊ ጹሁፎች በንጉስ አርማህ ታሪካዊ ተውኔት ላይ ያጠናሉ።

# ምዕራፍ ሶስት

# የመረጃ ትንተና

## 3. የነገስታት ገፀባህሪይ አሳሳል ንፅፅር ከ"ንጉስ አርማህ" እና "የመጨረሻዉ ንጉስ የቀ.ሀ.ስ " ታሪካዊ ተዉኔቶች አንፃር

### 3.1 የንጉስ አርማህ ታሪካዊ ተዉኔት ትንተና

#### 3.1.1 የንጉስ አርማህ ታሪካዊ ተዉኔት ጭምቅ ታሪክ

የንጉስ አርማህ ታሪካዊ ተዉኔት የሚከወነዉ በአክሱም ግዛት ዉስጥ ሲሆን በሰባተኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን ዉስጥ ነዉ። የንጉስ አርማህ ተዉኔት ታሪክ ሲጀምር የንጉስ ልጅ ልዑል ፍረሰናይ ከዉጭ ወራሪወች ጋር በመዋጋት ዳህላክን ነፃ አድርጎ ከቋሪሽ ተሰዳ ከመጣች፤ በፍቅር ከወደቀላትከ፣ ኢስላማዊት ኢም ሒበቡሀ ዘንድ በመሔድ እንዴት እንደናፈቀችዉ እና ስለጦርነቱ ሁኔታ እንዴት እንደነበር እየነገራት ይታያል ። ከልዑል ጋር አብሮ ዘምቶ የነበረዉ የንግስቷ ወንድም ጃን አፈላስ ጋር በመሆን ከንጉስ ፊት ይቀራረባሉ። ንጉሱም በተገኘዉ ድል ተደስቶ ለጃን አፈላስ የእድል አክሊል ፣ የአንድ አጥር እና ሽንጎ በመሸለም ለልጃቸዉ ልዑል ሰናይ የአባቱ ግዛት የነበረችዉን ኤደንን ነፃ እንዲያወጣት ያዝዘዋል ። በመቀጠልም ከድል ሲመለስ ቀጣዩ የአክሱም ንጉስ እንደሚሆንም ይነገረዋል ። የንጉስ የወንድም ልጅ የሆነዉ ጃን አስፈሀ የወደፊት የአክሱም ንጉስ የሚሆነዉ ልዑል ፍረ ሰናይ ስደተኛዋን ኢም ሒበቡሀን አግብቶ አክሱም እንደሚያረክሳት ስጋቱን ለአፈላስ ይነግረዋል ። የንጉሱ ሚስት ንግስቷም ልዑልን የወንድሟን ልጅ የሆነችዉ ናፓታን ከጦር ሲመለስ ለማግባት ብታስብም ሳይሳካላት ይቀራል። ንግስቷም የልዑሉን ጋብቻ አለመስማማት ሲያንገበግባት ከጃን አስፈሀ ጋር በመምከር ንጉሱን ዉጊያ ላይ እያለ በተመረዘ ወስፈንጠር ለመግደል ቢጥሩም አልተሳካላቸዉም። ልዑል ፍረ ሰናይ ኤደንን ነፃ አድርጎ ወደ አክሱም ሲመለስ የቋሪሽ ስደተኞች ወደ ሀገራቸዉ እንደተመለሱ ከንጉሱ ይሰማል ። ልዑል ፍረ ስናይም ከንጉስነቴ እሷ ትበልጥብኛለች በማለት ከአማካሪዉ ባሮክ ጋር በመሆን ኢም ሐበቡሀን ተከትሎ ይሔዳል ። ከተወሰኑ ቀናትም በኋላም ጃን አፈላስ ከኤደን ተመልሶ ወደ አክሱም በመምጣት ለንጉሱ ልዑል ባህሩ እያቋረጠ እያለ ጀልባ ተገልብጦ እንደሞተ ያስረዳዋል ። በመቀጠልም በወንስፈንጠር ለመግደል ሙከራ ያደረጉት ቤተ መንግስት ላይ ሲናገር ንግስቲቷ መርዝ ጠጥታ ትሞታለች። ንጉስ አርማህም ስልጣኑን ትቶ ደብረ ዳሞ ገዳም ይገባል። በዚህም መሰረት ተዉኔቱ ፍፃሜዉን ያገኛል።

#### 3. 1. 2 የንጉስ አርማህ ገፀባህሪይ ትንተና ከገጸባሃሪያት አሳሳል አንጻር

#### 3.1.3 የንጉስ አርማህ አካላዊ አሳሳል

የንጉስ አርማህ አካላዊ አሳሳል ብዙም በአጥጋቢ ሁኔታ አልተሳሉ።ከዕድሜቸው በስተቀር ፣ አቋማቼው፣ አለባበሳቸው ወ.ዘ.ተ.....አልተገለፀም። በትዕይንት 7 ገፅ 57

ንጉስ አርማህ ዕድሜያቸዉ አዛዉንት ሁነዉ ተስለዋል ።

ንጉስ አርማህ ፦… "እኔ አረጋዊ አባትህ ክንዴን ሳልተራስ አንተ ቀደምከኝ … ወሬ እኮ ነዉ።

የንጉስ አርማህ ካባ የሚለብሱ፣ ዘዉድ የሚጭኑ፣ ቡትረ ሙሴ የሚይዙ ሁነዉ ተስለዋል።

በትዕይንት 8 በገፅ 72 በሚከተለዉ ቃለ ተዉኔት ሰፍሯል።

ንጉስ አርማህ፦…(ካባቸውን ዘዉዳቸዉን በትረሙሴዉን አወላልቀዉ ያስቀምጡና ጥለዉ ይወጣሉ።)

## 3 . 1 . 4 የንጉስ አርማህ ማህበራዊ አሳሳል

ንጉስ አርማህ በተውኔቱ ውስጥ የንጉስ ካሌል የአበለዝ ልጅ የሀያሏ የአክሱም ንጉስ ነዉ ። ትዕይንት 2 ገፅ 6 ያለዉ ቃለ ተዉኔት ስንመለከት ፦

አጋፋሪ ፦ የሰማይ የምድር ጌታ በሆነዉ ዘላለማዊ አምላክ ሀያል አሸናፊ የሆነዉ

አርማህ የዳዊት ሰለሞን ልጅ የአልበዝ ልጅ የአክሱም ንጉስ ይናገራል ። (ያነባል )

ንጉስ አርማህ ንጉስ ከመሆኑ በፊት ወንድሙን ንጉስፁ በነበረበት ጊዜ የወንድሙ የጦር መሪ ነበር ።

ንጉስ አርማህ የክርስትና እምነት ተከታይ ሲሆን ሁል ጊዜ ድል ባስመዘገቡ ቁጥር ለፅዮን ማርያም ሀወልት ያቆማሉ ። በትዕይንት 2 ገፅ 8 ያለዉን ቃለ ተዉኔት ስንመለከት ፦

ንጉስ አርማህ ፦ … ይህ ዘመቻ በድል ከተወጣ ለልጃችን ለፅዮን ማርያም አባታችን የሰሩትን

ዓይነት ንሀወልት ልናቆምበት እንምላለን ። ቃላችን በአዋጅ እንዲነገር !!

በብራና ተፅፎ እንዲቀመጥ ይሁን ።(ተነስቶ ይሄዳል ጳጳሱ ይከተሉታል ።

ጭፈራዉ ይቀጥላል ። ልዑል ከበሮ ተቀብሎ በደስታ ይመታል ።)

በዚህ ቃለ ተዉኔት ዉስጥ የክርስትና እምነት ተከታይ ከመሆናቸዉ በላይ ለእምነታቸዉ ትልቅ ክብር እንዳላቸዉ እንዲሁም ቤተመንግስቱ ዉስጥ ጳጳስ እንዳለዉ ቃለ ተዉኔቱ ይጠቁመናል ። እንዲሁም ታሪኮችን በብራና አፅፈዉ ፣ ቃላትን ( መልዕክትን) በአዋጅ አስነግረዉ ፣ ሀወልት አቁመዉ ታሪክን እንዳይጠፋ የሚያደርጉ ንጉስ እንደሆኑ ተመልክተናል ።

ንጉስ አርማህ ከሰወች ጋር ጥሩ ግንኙነት የነበረዉ ከቋሪሽ ተሰደዉ የመጡትን ሙስሊሞችን ተቀብለዉ ሀገራቸዉ እንዲኖሩ ያገረጉ ንጉስ ናቸዉ ። በትዕይንት 7 ገፅ 58 ላይ ስንመለከት ፦

አጋፋሪ ፦…… ከነብዩ መሀመድ የተላከ !! ግዛትህ ወሰን የሌለዉ ፣ፍርድህም ቅን

የሆነዉ ንጉስ አርማህ ወገኖቼን እና ቤተሰቦቼን ሲሰደዱ አንተ ግን እጅህን

ዘርግተህ ተቀበልከኝ ። ሩህሩህ የአላህ ወዳጆችይ ይቀበሉህ !! ፈጣሪ በጠላቶቼ

ላይ ድል አቀናጅቶልኛልና በሰላም እና በተድላ ያኖርኳቸዉን ቤተሰቦችን

ስደድልኝ ።

አርማህ ፡- …ፈቅጃለሁ ሂዱ …

### 3.1. 5 የንጉስ አርማህ ስነ-ልቦናዊ አሳሳል

ንጉስ አርማህ የአባቶቹን ግዛት የነበረችውን ኤደንን ከፋሪሶች እጅ ነፃ ለማዉጣት ትልቅ ምኞት ነበረው ።ህይን ምኞቱን በልጁ ልዑል ፋሬ ሰናይ ያሳካዋል። በትይንት 2 በገፅ 7 ላይ ስንመለከት ፡-

አርማህ ፡- የአባታችን ግዛት የሆነችው የኤደን በፋሪሶች እጅ ከወደቀች ወዲህ

ወንድሞቻችን በባርነት የባህር ንግዳች በባዕዳን እጅ ወድቀዉብናል።

ባህር ተሻግሮ ኤደንን ወደ እቅፋችን መመለስ የአክሱም ታላቅ ህልም ነበር ።

ንጉስ አርማህ ለልጁ ፣ ለሚስቱ ወ/ክርስቶስ እንዲሁም ለሀገሩ ፋቅር ያለው ንጉስ ነው።በትይንት 4 በገፅ 33-34 ላይ ስንመለከት

ንጉስ አርማህ ፡- … ህዝቤን መንግስቴን እና አክሱምን የሚጎዳ

አንዳች ፀያፍስራ አንደማለሰራ ነው የማረጋገጥልህ።

ንጉስ አርማህ፡- .... በዛች ሴት ፍቅር ክፉኞ ወደቅሁኝ።

ባየኋት ቁጥር የአለትታህል እየከበደኝ የቋጥኝ ታህል

እየተጫነኝ ይመጣል ።…

ያቺ ሴት እናትህ ወ/ክርስቶስ ነበች።

በነዚህ ቃለ ተዉኔቶች ውስጥ ሚስቱን እንደሚያፈቅራት ይጠቁማል።

ንጉስ አርማህ የልጃቸው እናት የወ/ክርስቶስ ን ባለቤት በማስገደላቸው እሷ ይህን ስትሰማ በሀዘን ብዛት በፀፀት ስለ ሞተች ሁልጊዜ የሀዘን እና የፀፀት ስሜት ይሰማቸዋል። በትይንት 4 በገፅ 34 ላይ ስንመለከት

ፍሬ ሰናይ ፡- ፀፀት?

ንጉስ አርማህ ፡- አወ ፀፀት(በትካዜ) እናትህ ጃን ጎርጎርዮሰን እጅግ ታፈቅረው

ነበር ከእኔ ጋር በኖረችባቸዉ ስምንት አመታት ደስተኛ

አልነበረችም።በተለይ ጃን ጎርጎርዮስን በሚስጢር እንዳስገደልኩ

ስታዉቅ ሀዘኗ አንተን እንደወለደችም በፀፀት ብዛት አረፈች።

ንጉስ አርማህ የትካዜ ስሜት የሚያበዙ ፣ ብቸኛ እንደሚሆኑ ሁነው ተቀርፀው እናገኛቸዋለን።በትይንት 3 በገፅ 16-17 ስንመለከት

ፍሬ ሰናይ፡- .......ለምን የግሪክ ያነባል .........ለምን ደስተኛ ይሆናል

በትካዜ አለምን እንደ አባቱ አይመረምርም ( በሴት ቃና )

አለምን ምን ጎደላት ብየ ነዉ የምተከዘዉ ? ሰዉ እንደሆን

ምንግዜም ሰዉነቱ አይስት ።

ልዑል ፍረ ሰናይ እንጀራ ፍሬሰናይ እንደ አባቱ እንዲተክዝ ደስተኛ እንዳይሆን ትመኛለች። ደስታዉን ማየት

አትፈልግም ። ከዚህ ቃለተዉኔት ዉስጥ የምንረዳዉ አርማህ ሁልጊዜ እንደሚተክዝ ፣ ብቻዉን እንደሚያስብ እና ደስተኛ እንዳልሆነ እንረዳለን ።

በተጨማሪም ንጉስ አርማህ በጦርነት ጊዜ የሰዉ ደም እንደዲፈስ ሳይሆን ፍላጎታቸዉ አሸናፊነት ነዉ ። በትዕይንት 4 በገፅ 35 ላይ ስንመለከት ፡-

አርማህ ፡- …የወታደሮችን ጀግንነትማ መች ጠርጥሬ ብቻ ብዙ ደም

እንዳይፈስ…. የምንዋጋዉ ሰዉ ረክሶብኝ ሳይሆን የአባታችን ሀገር

የሆነዉን ከአባታችን ሀገር ከሆነዉ ጋር ለመቀላቀል ግድ ሆነብኝ ።

ንጉስ የወ /ክርስቶስን ባሏን አስገድሎ ካገባት በኋላ እሷ እንደማትወደዉ ሲያዉቅ በጣም እንደተፀፀተ፣ ጥሩ ስሜት እንዳልተሰማዉ በትዕይንት 4 ገፅ 35 ላይ ቃለ ተዉኔቱ ይጠቁመናል ፡-

ንጉስ አርማህ ፡-… ለእኔ ቅንጣት ፍቅር እንዳልነበራት

ሳዉቅ ምትኩ …የእዉነት ሞትኩ

## 3. 1.6 የ አርማህ የሞራልላዊ አሳሳል

ንጉስ አርማህ ለሰወች ክብር ያለዉ መሀሪ ይቅር ባይ ንጉስ ነዉ ። ጥፋተኛዉን ሰዉ እንደበደሉ ሳይሆን በደሉን እንዲማርበት ሚያደርግ ቅጣት ይቀጣል ። በትዕይንት 3 በገፅ 24 ስንመለከት ፡-

ግንበኛ ፡- ማንነትህን እናዉቃለን ባሮክ ድሮ ወንጀለኛ ዛሬ

ረዳት ግንበኛ መሆንህን እናዉቃለን ።" ንጉስ መሀረ ባይሆን ኑሮ "

ሲኦል ዉስጥ ከዳቢሎስ ጋር እሳት ትወረውር ነበር።

ንጉስ አርማህ ለሰወች ክብር ያላቸዉ እንደሆኑ በትዕይንት 2 በገፅ 8 እንዲህ ይገልፃል ፦

አርማህ ፦… ለደስታችሁ ወሰን አበጁለት ፣ ወዳየቤታችሁ ገብታችሁ

የሞቱትን ወታደሮች አስቡ … ድል እና ደም…(ይወጣሉ።)

በዚህ ቃለ ተዉኔት ዉስጥ በአለማዊም ሆነ በመንፈሳዊ ለሞት ሰዉ ተብሎ ክብር እንደሚሰጥ እና ነፍሳቸዉ እንድትማር ፀሎት እንደሚያደርግ ሁሉ ንጉሱም ይህን ህግ እያስፈፀመ ነዉ ።

ንጉስ አርማህ ለሰዎች መልካም እንግዳ አክባሪ ቅን የሆኑ ንጉስ ናቸዉ ። በትዕይንት 7

በገፅ 58 ላይ እንደሚከተለዉ ተገልፃል ።

ጃፈር ፦ እርግጥ ነው ታድላ ከፉ ሳይንካን አንዳች ሳይጎልብን

በሰላም ያኖረን ንጉስ ምን ዉለታ ይከፈለዋል ? ምንም !

የሰዉንም ስጦታ በምንም አይገኝም ብቻ ይህንን ስራ

ለልጅ ልጃቸዉ ለመላዉ ህዝብ የምንመሰክርበት ጊዜ እሩቅ አይሆንም።

ንጉስ አርማህ በሚስቱ በደል የፈፀመ የንስነቱን ስልጣን በመጠቀም የሰዉ ህይወት ያጠፉ እና የወ/ክርስቶስን ፋቅር የቀማ ሰው ሆኖ እናገኘዋለን ።

አርማህ፦ ንጉስ ስሆን በፍቅር የተዋጥኩበትን ሴት ለማግኘት እንደማያቅተኝ

በማመን ያን ጀግና ወታደር በሚስጥር አስገደልኩት ሚስቱንም

አገባሁ ይቺም ሴት እናትህ ናት ው፡ክርስቶስ ነበረች አንተንም

እንደወለደች በሀዘን እና በፀፀት ያለ እድሜ ሞተች

በዚህ ቃለ ተውኔት ውስጥ እንምንረዳው ንጉስ አርማህ በእሷላይም ሆነ በባለቤቷ ጎርጎርዬስ ላይ ትልቅ ጥፋት አጥፍቷል ። ሁለቱንም ከፍቅራቸዉ ለይቷቸዋል ። በሰራዉ ስራም ህይወታቸዉ አልፋል ። ይህ ስራዉ ራስ ወዳድነት ነዉ።

## 3.2 የመጨረሻ ንጉስ የቀ.ሀ.ስ ተዉኔት ትንተና

### 3.2.1 የመጨረሻ ንጉስ የቀ.ሀ.ስ ተዉኔት ጭምቅ ታሪክ

የመጨረሻው ንጉስ የቀ.ሀ.ስ ታሪካዊ ተውኔት መቼቱ የሚከናወንበት አዲስ አበባ በቀ. ሀ.ስ በተመንግስት ውስጥ፤በደርግ ቤት እና በቤተመንግስቱ ውስጥ በምትገኝ ትንሽዬ ክፍል ውስጥ ሲሆን ከ1966 ዓ.ም እስከ 1967 ዓ.ም ድርጊት ይፈጸማል።

ተውኔቱ የሚጀምረው በቀ. ሀ.ስ ቤተመንግስት ፅ/ቤት ውስጥ ወታደራዊ ደርግ የንጉሱን መኳንንት እና ሹማምንት እንዲሁም ዋና ዋና ባለስልጣናት የሚባሉትን እየያዘ በማሰሩ ሀገሪቱን በቤተመንግስቱ ባስከተለው ማህበራዊቀውስ ፣ ንጉስ ነገስት እና የንጉስ ነገስት ቤተሰቦችም ሆኑ ባለሙሎቻቸው በሙሉ ሁኔታዉ ግራ ተጋብተው የሀገሪቱ ኢታማዡር እና የደርግ ሊቀመንበር የሆነውን ሌ/ጀኔራል አማንን ጽህፈት ቤታቸው ድረስ በማስጠራት ሀሳባቸው ምንእንድሆነ እና እንዴትስ መቆም እንዳለበት ስጠይቁ ነዉ። ሌ/ጀኔራል አማንም ደርግ የሚባለው ወታደሩን የሚመራው አንድ ኮሚቴ ስለ ሆነ እና አንድ ግለሰብ ብቻውን የሚመራው ስለሆነ የመንግስት ዋና ዋና ዋና ባለስልጣናት እንዲታሰሩ የወሰነው ይህ ወታደራዊ ኮሚቴ እንደሆነ እና "ደርግ" የሚል መጠርያ ስምም እንዳለው ይነግራቸዋል።በመቀጠልም የደርግ ወታደራዊ ሀይል ህዝቡ በንጉሱ ላይ ያለችውን ፍቅር ሙሉ በሙሉ ለማክሽፍ የበለጠ ይረዳቸው ዘንድ በእንግሊዛዊው ጆናታን ድምቢልቢ ተቀርፆ የወሎ ረሀብ የሚያሳይ ፊልም ፤ ህፃናት የ እናታቸውን ደረቅ ጡት ሲምጉ ፤ አጥንታቸውና ቆዳቸው በአጠቃላ የንጉሱን አስነዋሪይ ተግባር የሚያጋልጥ ንጉስ በህዝብ ድርቀት እና ጉስቁልና ምንም እንዳልመሰላቸው የሚተርከው የፕሮፓጋንዳ ፊልም ለማየት ህዝቡ እንዲጠሏቸው አድርጓል።

ከዚያም በወታደሮች ከቤተመንግስት ወደ እስር ቤት ይወሰዳሉ። ሻለቃ መንግሥቱ ሃይለማሪያም ከስር ቤትም ንጉሱን ቤት በውጭ ሀገራት በድብቅ ብር እንዳስቀመጡና ያስቀመጡትን ገንዘብ ያለበትን እንዲጠቁመው መንግሥቱ ሃይለማሪያም ወትውተው ንጉሱም እንዳላስቀመጠው ደጋግሞ ይመልስለታል። ከዚያም በኋላ ምድርና የሚያስውጡት መስለው በትራስ አፍነው ይገድሏቸዋል። በመጨረሻም የቀ.ሀ.ስ አስከሬን ባለበት ጠገብ ሻለቃ መንግስቱ ኃይለ ማርያም ቀስ ብሎ ገብቶ የአንበሳ ስዕል ያለበትን "ሞአ፤ አንበሳ ፤ አም፤ ነገድ ይሁዳ፤ ስዮሙ፤ እግዚአብሔር፤ ዘ፤ ኢትዮጵያ" የሚለውን ፁሁፍ ያለበትን አረንጓዴ ቢጫ ፤ ቀይ ቀለም ሰንደቅ አላማ ያለብሳቸዋል። በዚህም መሰረት ተዉኔቱ ፍፃሜ ያገኛል።

## 3. 2.2 የመጨረሻዉ ንጉስ የ ቀ.ሀ.ስ ገፀባህሪይ ትንተና ከገጸባሃሪያት አሳሳል አንጻር

### 3.2.3.የቀ.ሀ.ስ አካላዊ አሳሳል

ቀ.ሀ.ስ የ82አመት አዛዉንት ሲሆን በጥዋት ሁልጊዜ አዘዉትረዉ የሚሊተሪ ቢጫ ልብስ እና ጫማ ሚጫሙ ናቸዉ። በተዉኔቱ ዉስጥ መጀመሪያ የገፀ ባህሪ መግለጫ ላይ ገፅ xi

ቀ.ሀ.ስ፡- ከ1992-1967 የኢትዮጲያ ንጉሰ ነገስት የነበሩ የ82 ዓመት የእድሜ ባለፀጋ

በገቢር 2 ትዕይንት 4 ገፅ 90 ላይ ስንመለከት፡-

ቀ.ሀ.ስ ፡- /ፈዛዛ ቢጫ ቀለም ያለዉ ሙሉ ''የሚሊተሪ'' ልብስ ይዞ ወደ ቆመዉ አሽከር ዙረዉ /

እርሱን አዘዉትረን ጥዋት ለስራ የምንለብሰዉን የሚሊተሪ ልብስ ዛሬ አንለብሰዉም።

ዛሬ ልብሳችንን እንለዉጣለን።

አገልጋይ ፡- ምን ለመልበስ ይወዳሉ እንግዲያስ ጃንሆይ?

ቀ.ሀ.ስ ፡- ሙሉ ልብሳችንን አዘጋጅልን።\ልብሳቸዉ እንደለበሱ እና ጫማቸዉ

እንደተጫሙ አሽከሮች ጎንበስ ቀና እያሉ ያግዟቸዋል።/

በገቢር 2 ትዕይንት1 ገፅ 64 ላይ በተጨማሪም ጃንሆይ ካቦርት ፣ቆብ፣ኩታ፣የሌሊት ልብስ ይለብሳሉ።

ቀ.ሀ.ስ ፡- |ቆቡን ጉልበቱ ላይ ይሳካል |

በገቢር 1 ትዕይንት 1 ገፅ 31 ቀሀስ ጠባብ አይን ያላቸዉ ሁነዉ ተስለዋል።

ቀ.ሀ.ስ ፡-..../ጠባብ አይናቸዉ የበለጠ አጥብበዉ /

በገቢር 2ትዕይንት 4 ገፅ 93 ላይ

ቀሀስ ፀጉራቸዉን የሚያበጥሩ ሁነዉ በተዉኔት ዉስጥ ተስሎ እንደሚከተለዉ እናገዋለን

ቀ.ሀ.ስ ፡- ማበጠሪያ አምጡልን | አገልጋይ ማበጠሪያ ይሰጣቸዋል። | ጫማችን በደንብ

ጥረግልን ( አገልጋይ ጫማቸዉን ይጠርጋል።)..... ካባችንን አቀብሉን( አገልጋዩ

ካባ አምጥቶ እንዲለብሱ ያደርጋቸዋል።

## 3.2.4 የቀ.ሀ.ስ ማህበራዊ አሳሳል

የቀ.ሀ.ስ ማህበራዊ አሳሳል ስንመለከት ቀ.ሀ.ስ እቴጌ መነን የተባሉ ሚስት አግብተዉ የሚኖሩ ፣ የ 61 ዕድሜ ያላት ተናኘወርቅ እና ልዑል መኮነን የተባሉ ሁለት ልጆች ያሉትእና እንዲሁም ብዙ የልጅልጅ ወልደዋል። የገፀ ባህሪያት መግለጫ ላይ ገፅxi በተዉኔቱ መጀመሪያ ገፅ ላይ የሚከተሉትን ቃለ ተዉኔቶች እነዚህ እዉነታዎች ያረጋግጥልናል።

ልዕልት ትናኘወርቅ ሀይለስላሴ ፡- የቀሀስ ልጅ እና የ61 ዓመት ወይዘሮ ከዚህ መግለጫ

ላይ የቀሀስ ሴት ልጅ መሆኗን ያረጋግጥልናል።

ልዕልት ሳራ ግዛዉ ፡-የቀሀስ ልጅ የሆኑት የልዑል መኮነን ሚስት፣

ከዚህ መግለጫ ላይ ልዑል መኮነን የሚባል ልጅ እንዳላቸዉ ይገልፃል።

በገቢር 3 ትዕይንት 4 ገፅ122

የልዕልት ትናኘወርቅ፣የልዑል መኮነን እናት እንደሆነች እና የቀሀስ ባለቤት እቴጌ መነን

መሆኗን በቃለ ተዉኔቱ ያረጋግጥልናል፡-

ልዕልት ትናኘ ወርቅ ፡- የእናቴን መነንን ፎቶግራፍ እንደሚፈልጉ ሰማሁ አምጥቼልሀለሁ።

በዚህ ቃለ ተዉኔት ላይ ሚስታቸዉ መነን እንደሆነች ይገልፃል።

በገፀ ባህሪያት መግለጫ ላይ በገፅ xi ላይ የቀሀስ የልጅ ልጃቸዉን እንደሚከተለዉ ይገልፃል፡-

ሪር አድሚረል ኮማንደር እስክንድር ደስታ ፡-የልዕልት ትናኘወርቅ ልጅ

ልዑል በእዳ ማርያም መኮነን ፡- የቀሀስ የልጅ ልጅ እና የ 17 አመት ወጣት

ልዑል ሚካኤል መኮነን ፡-የቀሀስ የልጅልጅ እና የ19 አመት ወጣት…ወዘተ

ሌሎችም ሲኖሩ እነዚህ ቃለ ተዉኔቶች ቀሀስ ብዙ የልጅ ልጅ እንዳላቸዉ ይገልፃል።

የቀሀስ የክርስትና እምነት ተከታይ ይህንንም የሚያረጋግጥልን በርካታ ቃለ ተዉኔቶች ሲኖሩ

ከነዚህም መካከል በገቢር 1 ትዕይንት 1 ገፅ 27ስንመለከት፡-

ቀ.ሀ.ስ ፡- እግዛብሔር ምህረት በጉነቱን ይላክላት ለክፉ እንደማይሰጠዉ ተስፋ እናደርጋለን

እንዲሁም በገቢር 1 ትዕይንት 1 ገፅ 25 ላይ ስንመለከት ፡-

ቀ.ሀ.ስ ፡- እንግዲ……የመገናኘታችን ምክንያት ምክር አድርገንበት አንተም

ጉዳዩን አጣርተንል ዙፋኑን በእግዛብሔር ፍቃድ ብንጠቀልለዉ

የሚበጅ ነገር ነዉ ብለን እናምናለን።

ቀሀስ የጤና ህይወታቸዉ ስንመለከት በክረምት ወቅትየሳል ህመም የሚያማቸዉ ንጉስ ናቸዉ።

በገቢር 1 በትይንት1 በገፅ 25 ላይ

ቀ.ሀ.ስ፡- ቅዝቃዜ ነዉ እንጅ ያን ያህል ለክፉ የሚሰጥ እንኳን አይደለ

ክረምት አይደል ወቅቱ አልፎ አልፎ ሳል ቢሰማን የተገባ ነዉ ብሎ ወሬ

ማድረጉ ልክ አይደለም። መስከረም ሊጠባ ትቂት ጊዜያት ነዉ የቀየሩት

አሁን እየሞቀ ሲሄድ ሳሉም ይተወናል።

ቀሀስ ኢትዮጲያን ለ14 ዓመት ደጃዝማች ሁነዉ ለ 44 ዓመት ንጉስ ሆነዉ ኢትዮጲያን ያገለገሉ ንጉስ ናቸዉ። ይህንን የሚያረጋግጥልን ቃለ ተዉኔት በገቢር 2 ትዕይንት 5 ገፅ 99 ላይ ስንመለከት ፦

ቀ.ሀ.ስ ፦ የምንወዳት ሀገራችንን በዳጅዝማችነት ለአስራአራት አመት ሲናገለግል ጦር ሰራዊቱ

ለሀገር የሰራነዉን ሁሉ ሳያዉቅ የሚቀር አልመሰለንም። የምንወዳትን ሀገራችን እና የሚወደንን

ህዝባችንን ለማገልገል ስንነሳ ስም ብቻ ተሸክመን አይደለም። (በስሱ ያስላሉ )

ከደጃዝማችነታችን ጀምሮ ሀገራችን እና ህዝባችንን ከአለም ጋር

ለማቀራረብ ጥረት አድርገናል። እንኳን የሀገራችን ህዝብ አፍሪካም አንድ የሚሆንበት

ተቋም አቁመናል። ህዝባችን የሚሰራበትን የሚማርበትን እና ቢያመዉ የሚታከምበትን ስፍራ

መስርተናል። በክፉ ግዜ ጠላትም ቢመጣ የሚመክትበትን አቅማችንን በፈቀደ

አደራጅተናል። እ… ለዚህ ደግሞ ከየ ክፍለ ሀገሩ ሰብስበን ደሞዝ ቆርጠን ሀገርን ከጠላት

እንድትመክቱ

ያቆምናችሁ እናንተዉ ወታደሮች ምስክሮች የምትሆኑ ይሆናል ?

በዚህ ቃለ ተዉኔት ዉስጥ ቀሀስ ምን ያህል ጊዜ ሀገራቸዉ እንዳስተዳደሯት ፣ ለማህበረሰቡ እንደ ንጉስነታቸዉ ማድረግ ያለባቸዉን የህክምና አገልግሎት ፣ ደንበር የሚጠብቅ ወይም ሀገር የሚጠብቅ ወታደር ማደራጀት ትልልቅን ተቋማት የመሰሰሉትን ስራ እንደሰሩ ይጠቁማል።

ቀሀስ በማህበራዊ ህይወቱ ጥሩ የሆነ ግንኙነት ያለዉ በተለያዩ ሀገርሮች ሽልማቶችን ያገኙ ንጉሱ ናቸዉ።

በገቢር 1 ትዕይንት 1 ገፅ 21 ላይ ፦

ሌ / ጄኔራል ፦ …… በቀሀስ የተጎበኙ ሀገሮች ዝርዝር……ይሔዉ ከመ

ሀምሳበላይ ነዉ። ይጎዛላብያ ፣በርማ ፣ ናይጀሪያ ……

( ወረቀቱን ገለጥ ገለጥ እያደረግን )ከሁለት መቶ በላይ ይበልጣል።

በገቢር 1 ትዕይንት 1 ገፅ 22 ላይ

ብ/ጀኔራልአሰፋ ፦ ……ቀ.ሀ.ስ.ሜዳሊያ የተሸሙባቸዉ ሀገሮች ዝርዝር……

ግሪክ፣እንግሊዝ፣ሞሮክ… ..ይሄም አይደለም የዶክተሬት

ያገኙባቸዉ ዩንቨርስቲወች…. ሃርቫርድ ፣ ሚቺጋን ……

በዚህ ቃለ ተዉኔት ዉስጥ ቀ. ሀ .ስ ከአገሮች ጋር ጥሩ ግንኙነት ስለ አለዉ ብዙ ሽልማቶችን እንደወሰዱ እና ማዕረግ እንዲሰጡ አድርጓቸዋል ።ቀሀስ ተንደላቀዉ የሚኖሩ ንጉስ እንደሆኑ ከሚከተለዉ ቃለ ተዉኔት በገቢር 1 ትዕይንት 4 ገፅ 56 እንመለከታለን ፡-

ሻለቃ መንግስቱ ፡- የንጉሱ የተንደላቀቀ ኑሮ ከተራዉ የወሎ ህዝብ ጋር

በጥሩ ሙዚቃ ተቀናብሮ በንፅፅር ሰርቷል

በዚህ ቃለ ተዉኔት ዉስጥ ንጉሱ ምንም ሳይጎልባቸዉ ተንደላቀዉ እንደሚኖሩ እና የእሳቸዉ የኑሮ ሁኔታ ከተራዉ ህዝብ የተሻለ እንደሆነ ይጠቁማል።

ቀ.ሀ.ስ በሚኖሩበት ቤተመንግስት ዉስጥ የተለያዩ ዘመናዊ የቤት ዕቃወችን ይጠቀማሉ። ስለዚህም እዉነታ በገቢር 2 ትዕይንት ገፅ 59 መግቢያ\ መግለጫ /ዉስጥ የሚከተለዉን ቃለ ተዉኔት እንመከታለን ፡-

- ቀ.ሀ.ስ ቤተ መንግስት ገበታ ቤት ዉስጥ ። ፊት ለፊት ፈዛዛ አረንጋዷዴ ቀለም ያለዉ የጠረጴዛ ጨረቅ የለበሰ ሰፊ የመመገቢያ ጠረጴዛ ይታያል። የ ወይን ጠርሙዞች፣

  የጠጅብርሌወች፣ጠጅ የተሞሉ የጠጅ ማቅረቢያወች እና ከብር

  የተሰሩ ሰሀ ኖች ተደርድረዋል።

### 3.2.5 የ ቀ.ሀ.ስ ስነ -ልቦናዊ አሳሳል

ቀ .ሀ .ስ ዉሻቸዉ ፣ ቤተሰባቸዉ ፣የስራ አጋራቸዉን እንዲሁም ሀገራቸዉን የሚወድ ሁነዉ እናገኛቸዋለን። በገቢር 2 ትዕይንት1 ገፅ30 እንደሚከተለዉ ተብራርቶ ቀርቧል ፡-

ራስ እምሩ ፡- ይሄዉ ደጋግመዉ አሰራቸዉ ። ለዚያዉም የሚወወዷቸዉን ልዑል

ራስ አስራተ ካሰን ፣ፀሀፈትዕዛዝ ተፈሪ ወርቅነህን እና

ሌሎቹን ጨምረዉ……

ቀ.ሀ.ስ ፡- |ትንሽ ከረርብለዉ |ታዲያ እነዚህ በደህና ግዜ የምንወዳትን

ሀገራችንን ሲያገለግሉ የነበሩትን የንግስና ዘዉዱን ………ጠብቀዉ

ያቆዩትን ወዳጆቻችንን መተዉ ነበረን……?

በተጨማሪ በገቢር 2 በትዕይንት 5 ገፅ 105 ላይ ስንመለከት ፡-

አገልጋይ ፡- ( በሀዘኔታ) ግርማዊነታቸዉ ዉሾቻቸዉ በጣም ነዉ ሚወዱት ……

እባካቹሁ ከሚመጡት መኪና ድረስይዘንላቸዉ እንምጣ……

በገቢር 2 ትዕይንት 1 ገፅ 61 ላይ

ቀ .ሀ. ስ ፡- ተክሎች ልክ እንደ ህፃናት የአይን ማረፊያ ብቻ ሳይሆን የፈጡር እስትንፋስም

ጭምር ናቸዉ።… ለዚያ ነዉ ተክሎች እና ህፃናትን የምንወድ…..

በዚህ ቃለ ተዉኔት ዉስጥ ቀ.ሀ.ስ ለህፃናት እና ተክሎችን እንደሚወዱ እንረዳለን።

ቀ. ሀ. ስ በታሰሩበት ጊዜ የልጃቸዉ ናፍቆት ያሰቃያቸዉ ነበር። በገቢር 3 ትዕይንት 1 ገፅ 110

ቀ. ሀ. ስ ፡- (ሊወጣ ሲል ) ትናኘወርቅ መጥታ እንድትጠይቀን አድርጉልን ።……

ልጆቻችን ናፍቀዉናል ። ልጆቻችንን አይናቸዉን ማየት እንፈልጋለን ።

ቀ. ሀ .ስ በታሰሩበት ጊዜ ተስፋ የመቁረጥ እና የመድከም ስሜት ይታይባቸዉ ነበር። በገቢር 3 ትዕይንት 4 ገፅ 122

ልዕልት ተናኘወርቅ ፡- (እያለቀሰች )…… ልጄን እስክንድርን …… ገደሉብኝ …

እርስዎ ግን ደህናነዎት?...(ዝም ይላሉ።)…ደህና ምግብ

ያገኛሉ ? እስኪ ………እንዴት ነዉ የእስሩ ኑሮ ?

ቀ. ሀ. ስ ፡- ( ዝም ብለዉ ይቆዩና ) …… አሁን ደክሞኛል ……… አሞኛል ።

## 3.2.6 የቀ.ሀ.ስ ሞራላዊ አሳሳል

ቀ .ሀ. ስ ሽፍታናቸዉ ብለዉ ባስገደሏቸዉ አርበኞች ይፀፀቱ ነበር ። አምላካቸዉንም ይቅርታ እንዲያደርጉላቸዉ ፈታርያቸዉን ይለምኑት ነበር።

በ ገቢር 3 ትዕይንት 3 ገፅ118 ላይ

ሻለቃ መንግስቱ ፡- ( አትክሮ እየተመለከታቸዉ ) ልክ እርስዎ ሽፍታ ናቸዉ ብለዉ

ባስገደሏቸዉ አርበኞች … እንደሚፀፀቱት ?

ቀ .ሀ .ስ ፡- አንድም አርበኛ እንዲገደል አልወደድንም ነበር ።

ሻለቃ መንግስቱ ፡- (በፍጥነት) ግን ፈቅደዋል ። … ግርማዊነትዎ ፈቅደዋል እኮ

ቀ.ሀ.ስ፡-ፈጣሪያችንን ይቅርት ለምነናል ።

በዚህ ቃለ ተዉኔት ዉስጥ ቀ.ሀ.ስ የአለማዊዉም ሆነ የመንፈሳዊ ህግ የማይፈቅደዉን ጥሰዉ ንፁህ አርበኞችን አስገድለዋል። ይህ ከንጉስ ሆነ ከሌላ ሰዉ የሚጠበቅ አይደለም።

## 3.3 የንጉስ አርማህ እና የንጉስ ቀ.ሀ.ስ የገፀባህሪይ አሳሳል ንፅፅር እና ግምገማ

ከዚህ በፊት ቀደም ብሎ የሁለቱን ነገስታት ገፀባህርያት ከገፀባህርያት አሳሳል ተመልክተናል። የሁለቱን ነገስታት የገፀባህሪይ አሳሳል ንፅፅር ስንመለከት፡- አካላዊ አሳሳል በንጉስ አርማህ ስለ እድሜቸው እና ስለ አለባብሳቸዉ ተገልጿል። ንጉስ አርማህ አዛዉንት እንደሆኑ አለባብሳቸዉም ካባ እንደሚለብሱ፣ ዘዉድ እንደ ሚጭኑቷ እንዲሁም በትረ ሙሴ እንደ ሚይዙ ተገልጿል። የቀ.ሀ.ስን ስንመለከት የሚሊተሪ ልብስ፣ ኩታ፣ ቆብ፣ ካቦርት እንደሚለብሱ፣ፀጉራቸዉ ሽበት እዳለዉ እና እንደሚያበጥረው ተገልጿል። በሁሉቱም ገፀባህሪያት ውስጥ በቂ የሆነ የገፀባህርያት አሳሳል ገለፃ አለ ማለት ባያስችልም የቀ.ሀ.ስ ገፀባህሪይ በበለጠ ሁኔታ ተገልፆ እናገኝዋለን። የንጉስ አርማህ ግን አካላዊ ማንነቱ በበቂ አልተገለፀም።

ወደ ማህበራዊ አሳሳል ስንመጣ ስለ ሁለቱ ንጉሶች ስለ ቤተሰባቸዉ፣ ስለ ስራቸዉ፣ ስለ ማህበራዊ እንቅስቃሲያቸዉ፣ ስለ እምነታቸዉ በበቂ ተገልጿል። የንጉስ አርማህ የቤተሰብ ሁኔታ፣ የበፊት ስራዉ ምን እንደነበር፣ ስለ ማህበራዊ ግንኙነታቸዉ የተገለፀ ሲሆን የቀ.ሀ.ስም እንዲሁ ስለ ቤተሰቡ፣ስለ እምነቱ፣ በፊት ምን አይነት ስራ እንደነበረዉ፣ ከሀገሮች ጋር ስላለዉ ግንኙነት በጥሩ ሁኔታ ተገልጿል።

በሁለቱ ገፀባህርያት ዉስጥ የማህበራዊ አሳሳል ትኩረት በመሰጠት ተገልፆ እናገኝዋለን። ስለዚህ ሁሉቱም ገፀባህሪያት በማህበራዊ አሳሳላቸዉ ጥንካሬ ይታይባቸዋል።

የስነልቦናዊ አሳሳል በምንመለከትበት ጊዜ የንጉስ አርማህ የሚወዱትን፣ የሚሰማቸዉን ስሜት፣ እምነታቸዉን እና ፍላጎታቸዉ በደንብ ተገልጿል። እንዲሁም የቀ.ሀ.ስን ስንመለከት የሚወዱትን እና የሚሰማቸዉን ስሜት ተገልጿል።

በሁለቱ ስነልቦናዊ አሳሳል የገፀባህርያቱ ማንነት ሲገለፅ ትኩረት ተሰጦት የተገለፀዉ የንጉስ አርማህ ገፀባህሪይ ሲሆን የቀሀስ ግን ውስን ነው።

በመጨረሻም የሞራላዊ አሳሳል ስናይ አርማህ ለሰወች ስላለው ክብርእና በሚስቱ ላይ ስለፈፀመባት በደል ሲገለፅ እንዲሁም የቀ.ሀ.ስ በሰወች ላይ ስላደረሰዉ በደል ተገልጿል።

ሁለቱንም ገፀባህሪያት አሳሳላቸዉን ስንመለከት በደንብ ትኩረት ተሰጦት አልተገለፀም። ይህም ማለት በሁለቱም ገፀባህርያት ሞራላዊ አሳሳል ላይ መገለፅ ያለባቸዉ ነገሮች አልተገለፁም።

# ምዕራፍ አራት

# 4 ማጠቃሊያ እና የመፍትሔ ሀሳቦች

## 4.1 ማጠቃለያ

በዚህ ጥናታዊ ፁሁፍ የነገስታት ገፀባህሪ አሳሳል ንፅፅር በንጉስ አርማህ እና በመጨረሻዉ ንጉስ ቀ.ሀ.ስ. ታሪካዊ ተዉኔቶች አንፃር በመተንተን ፣ በማነፃፀር እና በመገምገም ለመዳሰስ ተሞክራል ። በዚህ መሰረት በዉስጡም ታሪክን ፣የታሪካዊ ተዉኔትን ምንነትን ፣ የንፅፅር ጥናት ምንነት ፣ የገፀባህሪያት ምንነት ፣ ስለ ገፀባህርያት አሳሳል ፣ የሁለቱ ታሪካዊ ተዉኔት ጭምቅ ታሪክ ፣ የነገስታት ገፀባህሪይ አሳሳል ፣ የገፀባህሪያት አሳሳል ንፅፅር እና ግምገማን አካቶ ለመዳሰስ ተሞክሯል። የነገስታቱ ገፀባህሪ በገፀባህሪያት አሳሳል ሲተተነተኑ ንጉስ አርማህ እድሜቸው አዛውንት ሲሆኑ በ7ተኛው መ/ክ/ዘመን አክሱምን ሲያስተዳድሩ የነበሩ ንጉስ ናቸው። ንጉሱ ሀገራቸውን፣ ቤተሰባቸውን፣ ህዝባቸውን፣ ልጃቸውን የሚወዱ ንጉስ ናቸው። የአባታቸው የነበረውን የኤደንን ግዛት ከፋሪሶች ነፃ ለማዉጣት ፍላጎት የነበራቸዉ ፣በጦርነት ጊዜ የሚፈልጉት የሰው ደም እንዲፈስ ሳይሆን አሸናፊነትን ነው። ንጉሱ ሁለት ሚስት አግብተው የነበሩ ሲሆኑ የልጃቸው እናት የነበረችዋን ወ/ክርስቶስን ያፈቅሯት ነበር። ከሰወች ጋር ጥሩ ግንኙነት ያላቸው ፣ሰወችን የሚያከብሩ ፣በሚወዷት ሚስታቸው በመሞቷ ሚፀፀቱ ሲሆኑ እነዚህ ሁሉ መግለጫውች አርማህን ይወክሉልናል። የቀ.ሀ.ስንም ስንመለከት ቀ.ሀ.ስ የ82 አመት አዛውንት፣ ሽበት ያላቸዉ ፣ፀጉራቸውን የሚያበጥሩ ፣ የሚሊተሪ ልብስ አዘውትረው የሚለብሱ፣ ትንንሽ አይኖች ያሏቸው፣ የሳል በሽታ ያለባቸው ንጉስ ናቸው። ኢትዮጵያን ለ 44 አቶ ያስተዳደሩ፣ የክርስትና እምነት ተከታይ የሆኑ፣ ከሰወች ጋር ጥሩ ግንኙነት ያላቸው፣ ልጆችና የልጅ ልጆች ያላቸው ፣ሀገራቸውን ቤተሰባቸውን የሚወዱ፣ ለሰወች ክብር ያላቸው፣ በስህተት ባስገደሏቸው አርበኞች የሚፀፀቱ፣ የሳል በሽታ ያለባቸዉ ከሁሉም የአሳሳል መንገዶች በተሻለ የተተነተነ በማህበራዊ አሳሳል ላይ ነው። ይህም ማለት ማህበራዊ ሙሉ ለሙሉ ተገልጿል ለማለት አያስደፍርም። በተጨማሪም በንጉስ አርማህ ታሪካዊ ተዉኔት ዉስጥ ያለዉ የንጉስ አርማህ አካላዊ አሳሳል በደንብ ሁነዉ አልተሳሉም ።በአጠቃላይ ይህ ጥናታዊ

ፁሁፍ በሁለቱ ታሪካዊ ተዉኔቶች ዉስጥ ያሉትን ነገስታት ገፀባህሪያት ከገፀባህርያት አሳሳል ደረጃ በመተንተን ፣ በማነፃፀር እና በመገምገም የተሰራ ነዉ ።

## 4.2 የመፍትሔ ሀሳብ

አጥኝዋ ይህን ጥናታዊ ፁሁፍ በምታጠናበት ወቅት በሁለቱም ተዉኔት ዉስጥ ያሉትን በሁለቱ ነገስታት ገፀባህሪይ አሳሳል ላይ ትቂት ጉድለቶችን ለመመልከት ችላለች። ሁለቱም በአካላዊ ፣ በማህበራዊ ፣ በስነልቦናዊ ፣ እና በሞራላዊ የገፀባህሪይ አሳሳል ንፅፅር ተተንትነዋል። የአርማህ አካላዊ ማንነቱ በደንብ አለመገለፁ ለአንባቢያን አካላዊ ማንነቱ ግልፅ ሳይሆን ይቀራል ። ይህም አካላዊ አሳሳሉ ግልፅ ቢሆን ኑሮ አንባቢያንም ተዉኔቱን የበለጠ እንዲረዱት ወይንም የአርማህ ገፀባህሪ አካላዊ ማንነት ከአእምሮቸዉ እንዲቀረፅ ያደርግ ነበር። እንዲሁም የማህበራዊ አሳሳላቸዉ በደንብ መገለፁ ለአንባቢያን ሁለቱ ንጉሶች ማህበራዊ ህይወታቸዉ እንዴት እንደሆነ ለማወቅ ይረዳል ነበር ።በአጠቃላይ ተዉኔቶች ሲፃፈ ገፀ ባህሪያት ግልፅ በሆነ መልኩ እና ሁሉም በገፀባህሪይ አሳሳል ደረጃወች ጥሩ ሁነው ቢገለፅ፣ አንባቢያን ተዉኔቶችን ለማንበብ እንዲነሳሱ እና የተሻለ እንዲረዷቸዉ ለማድረግም ይረዳል ።ስለዚህ በተዉኔቱ ዉስጥ ያሉትን ገፀ ባህሪያት የእዉነት በአለም ላይ እንዳሉ አስመስለዉ መሳል፣ የአንባቢያን ቁጥር ከፍ ለማድረግ እና የአንባቢያንን የንባብ ልምድ ለማዳበር ያስችላል።

## ዋቢ መፅሐፍት

ዘሪሁን አስፋዉ ።(1998 ) ። የስነፁሁፍ መሰረታዉያን ፣አዲስ አበባ ፣ንግድና ማተሚያ ቤት ።

የሻዉ ተሰማ ።(1990) ። የተዉኔት አፅናፍ መነፀር ፣አዲስ አበባ ፣ ኩራዝ ኢንተርፕራይዝ ድርጅት ።

ፋንታሁን እንግዳ ። (1990 )። ዝክረ ተዉኔት ፣ አዲስ አበባ ፣ ብርሀን እና ሰላም ማተሚያ ቤት ።

________________።( 1993 ) ። የተዉኔት አፃፃፍ ዘዴ ፣ አዲስ አበባ ፣ ብርሀን ና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ።

________________።(1993)። ከሀ እስከ ፐ፣ አዲስ አበባ፣ብርሀን ና ስላም ማተሚያ ድርጅት።

እንዳለ ም አስቻለው።(2010)። ንግስት ዘውዲቲ ታሪካዊ ተውኔት፣ብርሀን እና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

ያለዉ እንግዳወርቅ ሙሉ ። ( 1998 ) ። የምርምር መሰረታዊ መርሆወች ና አተገባበር ባህርዳር ዩንቨርስቲ።

አለም እሸቱ ።(1994)።መሰረታዊ የምርምር እና የዘገባ አፃፃፍ ፣ አዲስ አበባ ፣ የቅድስት ማርያም ኮሌጅ
የሊበራል አርትስ

ፋክሊቲ ህትመት ።